# ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ቁልፍ የረቂቅ ሕጉ ድንጋጌዎች እና ከሲቪል ማህበረሰቡ የቀረቡ ማሻሻያ ሀሳቦች

**ህዳር 2001**

## 1. *የመደራጀት መብት*

### 1.1 "ኢትዮጵያዊ፣ የኢትየጵያ ነዋሪዎች" እና "የውጭ" የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ትርጉም፡- አንቀጽ 2(2)፣(3)፣(4)

ይህ ድንጋጌ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን የገቢ ምንጫቸውን መሠረት በማድረግ የድርጅቶቹን ማንነት ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ የአንድ ድርጅት ወይም ማህበር አገራዊነት ሊታይ የሚገባው በተመዘገበት ወይም መደበኛ ሥራውን በሚያከናውንበት ሥፍራ መሆን አለበት እንጂ በገቢ ምንጭ መሆን የለበትም፡፡ እንደዚህ አይነት ተሞክሮም የለም፡፡ የገቢ ምንጭን መሠረት በማድረግ የመደራጀት መብትን መፍቀድ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 31 ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

በሕጉ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው የዚህ ሕግ ዋንኛ ዓላማ በአድ እና ማህበራት በኢትዮጰያ ህዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለመደገፍና ለማሳለጥ ነው፡፡ ሥለዚህ ኢትዮጵያዊ የሆኑ በአድ እና ማህበራት ከውጨ የሚያገኙት የገቢ መጠን ከ10% መብለጥ የለበትም ሲባል በቅድሚያ እነዚህን ተቋማት አሁን ካሉበት ደረጃ በተሻለ ሊያሠራቸው የሚያስችል የአገር ወስጥ የገቢ ምንጭ መኖሩ ወይም እንዲያገኙ የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታ መፈጠሩ መረጋገጥ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ሕጉ ገደቡን ከማስቀመጥ በቀር የፈጠረው አንድም የተመቻቸ ሁኔታ የለም፡፡ታይህ አንቀጽ በማህበራቱ ገቢ ላይ ብቻ ሣይሆን በሚከተሉት አበይት ምክንያቶችም እንደገና ሊጤን ይገባዋል፡፡

- ከ10 በመቶ በላይ ገቢያቸውን ከውጭ እርዳታ በማግኘት በልማት እና በዲሞክራሲ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ያሉትን እና በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን አብዛኛዎቹን ሀገር በቀል ድርጅቶች ኢትዮጵያዊ ማንነት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ እና ህገመንግስታዊ የሆነውን የመደራጀት መብት የሚጥስ በመሆኑ፣
- የተቋማቱ የገቢ ምንጭ ከዜጎች የመደራጀት መብት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው በመሆኑ፣

- ከአንቀጽ 16(6) ጋር ተጣምሮ ሲነበብ አብዛኞቹ ሀገር በቀል ድርጅቶች በልማት ፖሊሲ ተሟጋችነት፣ በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ፣ በዲሞክራሲ ግንባታ፣ እና ግጭቶችን በመፍታት እንዲሁም በዜግነት እና ማህበረሰባዊ ልማት ስራዎች በጥቅሉ በፖሊሲ እና መልካም አስተዳደር ስራዎች የሚያደርጉትን ከፍተኛ ተሳትፎ እንዲያቆሙ የሚያስገድድ ስለሆነ እና ይህም በሀገሪቱ በመገንባት ላይ ያለውን ዲሞክራሲ እና ልማት በእጅጉ የሚጎዳው ከመሆኑም በላይ የተጠቃሚዎች መብትን ስለሚጻረር፤
- አንቀፁ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰቡን እድገት (እለታዊ እርዳታ ከማቅረብ ወደ ማህበራዊ አገልግሎት፣ ከዚያም መብት ተኮር ወደሆነ የልማት እንቅስቃሴ እና ተሟጋችነት) ወደኋላ በመቀልበስ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ለልማት እና ዲሞክራሲ መጎልበት ወሳኝ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች ተቆጥበው በእርዳታ እና አገልግሎት አቅርቦት ላይ ብቻ እንዲወሰኑ የሚያደርግ አሉታዊ ውጤት ያለው በመሆኑ ፤
- ከአንቀጽ 74(1) (ሠ) ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ከገቢያቸው 10% በላይ ከውጭ የሚያገኙት ብዙሀን ሀገር በቀል ማህበራት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይመዘገቡ እና ህጋዊ ሰውነት እንዳያገኙ ስለሚከለክል፤
- በአንቀጽ 118 (3) መሠረት እነዚህ ሀገር በቀል ድርጅቶች በኤጀንሲው ውሳኔዎች ላይ ለፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብታቸውን እንዲነፈጉ ስለሚያደርግ፤

በመሆኑም ይህ ድንጋጌ በሚከተለው መልኩ ሊስተካከል ይገባዋል፡፡

*የኢትዮጵያ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ማህበር ማለት በኢትዮጵያ ህግ መሠረት የተመሠረተ፡ በኢጥዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚሰራና ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ማለት ነው፡፡*

## 1.2 ምዝገባን በሚመለከት አንቀጽ 69 እና 70

የብዙ አገራት ልምድ እንደሚያሳየው የመደራት መብትን አደጋ ላይ ከሚጥሉ መሰናክሎች ውስጥ አንዱና ዋንኛው የምዝገባ ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ስርዓት በአግባቡ ካልተያዘ መብቱን የመንፈጊያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል፡፡ በረቂቅ ህጉ ላይ ምዝገባን አስመልክቶ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ ግልጽነት የሚጎድላቸውና ለትርጉም በር የሚከፍቱ ሥላሉ እነዚህ ግልጽ ሆነው መቀጥ አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፤

- ኤጀንሲው በህጉ ላይ በተመለከተው በ30 ቀናት ውስጥ የምዝገባ ሠርተፊኬት ካልሰጠ ወይም የማይሰጥ መሆኑን ካላሳወቀ አመልካቹ ድርጅት እንደተመዘገበ የሚቆጠር መሆኑ መመልከት አለበት፡፡

- ለኤጀንሲው ለምዝገባ የሚያስፈልጉ በስም ያልተጠቀሱ ሰነዶችን የመጠየቅ ስልጣን ሊሰጠው አይገባም፡፡
- ምዝገባ መከልከል ያለበት አመልካቹ ችግሮችን እንዲያስተካክል በቂ እድል ከተሰጠው በኂላ መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም ክልከላው መሆን ያለበት በግልጽ ተለይተው በታወቁ ከባድ ጉዳዮች ላይ ብቻ መሆን አለበት፡፡

### 1.3 የክልል ውክልና፡- አንቀጽ 58

የመደራጀት መብት በውስጡ ከሚይዛቸው መብቶች ውስጥ አንዱና ዋንኛው በዓላማ ከሚመሳሰሉት ማንኛውም ሰው ጋር በፍላጎት መሰባሰብን ነው፡፡ አንድ ድርጅት አገራዊ ሥያሜ ሥላለው ብቻ እንደ ሕብረ ብሄር የፖለቲካ ፓርቲ በሥሙ ለመጠቀም ክልላዊ የኣባለት ውክልና ያስፈልግሃል ተብሎ መገደዱ በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠውን የመደራጀት መብት በእጅጉ ይጎዳል፡፡ የአባለት ዓይነትና ቁጥር መወሰን ያለበት በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት እንጂ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሆን የለበትም፡፡ አድራጎቱም በማኅበራቱ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንደ መግበት የሚያስቆጥርና መብቱን በተለያዩ ክልል ላይ ኀደኛ ወይም የሚያውቁት ሰው ላላቸው ወገኖች ብቻ የሚሰጥና ሌሎች ወገኖችን የሚያገል ያደርገዋል፡፡ ይህ ገደብ በረቂቅ ህጉ ላይ መቀመጡ ለምን እንዳስፈለገና የሚጠብቀውም ህጋዊና ሕዝባዊ ጥቅም ምን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ገደቡ የመደራጀት መብት ላይ ሊጣሉና አለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ገደቦች መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ ሥለዚህ ይህ ገደብ ሊነሳ ይገባዋል፡፡

### 1.4 ገቢ፤ታክስ እና የመንግሥት ድጋፍ

ከመደራጀት መብት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ዓቢይ ጉዳይ ድርጅቶቹ ለተቋቋሙባቸው ዓላማዎች ማስፈጸሚያ የሚሆን ገቢ ለማግኘት ያላቸው እድል ነው፡፡ ይህንን ገቢ ከአባሎቻቸው ወይም ሥራዎቻቸውን ከሚደግፉ ግለሰቦችና ተቋማት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ በተለይም ለሦስተኛ ወገኖች ጥቅም የተቋቋሙ ድርጅቶች ሥራቸውን በሚገባ ለመወጣት ሰፊ የገቢ ምንጭ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ረቂቅ ህጉ ካሉት ጠንካራ ጎኖች ውስጥ አንዱ በአንቀጽ 104 ላይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ መሠማራት እንደሚችሉ መፍቀዱ ነው፡፡ ሆኖም የዚህን አንቀጽ ጠቀሜታ ሥንመለከት አንቀጹ በቅድመ-ሁኔታዎች የተሞላ ከመሆነም በላይ የሚሰጠው የተለየ ጥበቃ የለም፡፡

ህጉ በተለይ ለኢትዮጵያውያን ድርጅቶች በአንድ በኩል ከውጭ ዕርዳታ እንዳያገኙ ከፍተኛ ገደብ አስቀምጦ እነዚህ ተቋማት የገንዘብ አቋማቸውን የሚያጠናክሩበት ምንም ዓይነት ምቹ ሁኔታ አለመፍጠሩ ችግሩን ከባድ ያደርገዋል፡፡ የሌሎች አገራት ልምድ እንደሚያሳየው መንግሥት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በተለያየ መንገድ ያበረታታል፡፡ ለምሳሌ ከተወሰኑ የታክስ ዓይነቶች ነጻ በማድረግ እና ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት፡፡ ረቂቅ ህጉ ግን ገደብ ከማስቀምጥ ውጭ የሚሰጠው የተለየ ምቹ ሁኔታ የለም፡፡

## *2. ሕጋዊ በሆኑ ሥራዎች ወይም ዓላማዎች ላይ የመሰማራት መብት*

### 2.1 "የውጭ" እና "የኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች" ተብለው ለተመደቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የተከለከሉ ሥራዎችን በሚመለከት፡- አንቀጽ 14

በዚህ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 5 መሠረት "የውጭ" እና "የኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች" ተብለው የተመደቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከዚህ በታች በተመለከቱት ሥራዎች ላይ መሰማራት እንደማይችሉ ተመልክቷል፡፡ እነዚህም

- በሰብአዊና ዲሞክራሲያዉ መብቶች፣
- የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ የጾታና የሃይማናት እኩልነት መረጋገጥ በማበረታታት፣
- የህፃናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን በማበረታታት፣
- የግጭት አፈታት ወይም እእርቅን በማስፋፋት፣
- የፍትህና የህግ ማስፈፀም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት በማጠናከር ሥራ

ሆኖም ይህ ክልከላ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 31 እና የአለም አቀፉን የሲቭልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ሥምምነት አንቀጽ 22 የሚቃረን ነው፡፡ ሕገ መንግስቱ ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ሕጋዊ ዓላማ የመደራጀት መብት ያለው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ እነዚህ ከላይ የተመለከቱት ሥራዎች ደግሞ ህጋዊ ዓለማዎች ለመሆናቸው የሚያጠራጥር ነገር የለም፡፡ ሥለዚህ "የውጭ" እና "የኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች" ተብለው የተመደቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በእነዚህ ሕጋዊ ሥራዎች ላይ እንዳይሰማሩ መደረጉ ህገ መንግሥቱን እና የአለም አቀፉን የሲቭልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ሥምምነት ስለሚቃረን ክልከላው ሊነሳ ይገባዋል፡፡

### 2.2 ለኢትዮጵያውያን ብዙሃን ማህበራት የተሰጠው ልዩ መብት፡- አንቀጽ 58

ይህ ድንጋጌ ለ"ኢትዮጵያውያን ብዙሀን ማኅበራት" ለይቶ በምርጫና ዲሞክራሲያዊ ሥራዎች ላይ መሠመራት እንደሚችሉ መግለጹና ተመሳሳይ መብት ለሌሎች ያለመስጠቱ አድሎአዊ ያደርገዋል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ልዩነት ለመፍጠር ያስፈለገበት ሕጋዊ ምክንያትም ግልጽ አይደለም፡፡

በተጨማሪም ይህ ድንጋጌ በ1999 ዓም የወጣውን እና የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ሥልጣን የሚወስነውን አዋጅ የቃረናል፡፡ በምርጫ ሕጉ መሠረት በምርጫና በሥነ ዜጋ ትምህርት ላይ እነማን መሳተፍ እንዳለባቸው ለመወሰን ሥልጣን የተሰጠው ለቦርዱ ነው፡፡ ሆኖም ረቂቅ ህጉ ይህን ሣያገናዝብ ኢትዮጵያውያን ብዙሀን ማኅበራት በምርጫ ሂደት ውስጥ መሳተፍ እንደሚችሉ ያስቀምጣል፡፡

2.3 የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች፡- አንቀጽ 62

ይህ ድንጋጌ በድርጅቶችና ማህበራት የውስጥ ጉዳይ ኤጀንሲው የማያስፈልግ ጣልቃ እንዲገባ የሚጋብዝ ነው፡፡ የጠቅላላ ጉባኤ ሥብሰባ ሊጠራ ያልተቻለበትን በቂ ምክንያት እንኳን ሣያጣራ ከአባላት አንድ ሰው ስለጠየቀ ብቻ የግዴታ ሥብሰባ እንዲጠራ መደረጉ እና የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ በኤጀንሲው መሾሙ አግባብ አይደለም፡፡ የአባላት መሪዎቻቸውን የመምረጥ መብት ሊነፈጉ አይገባም፡፡

## *3. ፍትሕ የማግኘት መብት*

**3.1 አቤቱታና ይግባኝ፡- አንቀጽ** 104

በህገ መንግሥቱ በአንቀጽ 37 ላይ ፍትህ የማግኘት መብት ዜግነትን መሠረት ሳያደርግ ለማንኛውም ሰው በእኩል ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ የረቂቅ ህጉ አንቀጽ 104 ይህንን መብት ለኢትዮጵያውያን ብቻ በመገደብ አስቀምጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ህገ መንግሥቱ ፍትህ የማግኘት መብትን ሲያረጋግጥ በማንኛውም በዳኝነት አካል ሊታይ በሚችል ጉዳይ ላይ ሲሆን ረቂቅ ህጉ በተቃራኒው ይህንን መብት በመገደብ በሕግ ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ምንም ዓይነት የዳኝነት ሥልጣን በሌለው አካል በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ እንዳይጠየቅ መደረጉ ሕገ መንግሥታዊ አይደለም፡፡

በመሆኑም የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 104 ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 አኳያ ታይቶ ኤጀንሲው በሚሰጣቸው የመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት እንደሚቻል መመልከት አለበት።

### 3.2 ቅጣት አንቀጽ 103

መብትን በመጠቀም ረገድ ሕግን በመተላለፍ የሚጣሉ ቅጣቶች ከአስተማሪነታቸው አልፈው ሰዎች በመብቶቻቸው እንዳይጠቀሙ የሚያሸማቅቁና የሚያስፈሩ መሆን የለባቸውም። ቅጣትን አስመልክቶ እስካሁን በቀረቡት ረቂቆች ላይ መሻሻል የታየ ቢሆንም አሁንም በረቂቅ ሕጉ ላይ የተመለከተው የቅጣት መጠን በአገራችን ካሉ ሌሎች የሕግ መተላለፍ ቅጣቶች አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ነው። የሕጉን ተላላፊዎች በንኡስ ቁጥር 1 ላይ እንደተመለከተው አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሠረት መጠየቅ በቂ ሥለሆነ ንኡስ ቁጥር 2 ሊሰረዝ ይገባዋል።

### 4. የአስተዳደር አካላትን በሚመለከት

ረቂቅ ህጉ ዘርፉን የሚመለከት አራሱን የቻለ አስተዳደር እንዲመሠረት ማድረጉ ከጠንካራ ጎኖቹ ውስጥ አንዱ ነው። ይሁን እንጂ ለአስተዳደር አካላት የሚሰጠው ሥልጣን የዘርፉን ነፃነትና ተጠያቂነት በአንድነት የሚያስተናግድ እንጂ ቁጥጥርን ብቻ መሠረት ያደረገ መሆን የለበትም። ከዚህ በተጨማሪ የአስተዳደር አካሉ ነጻና ገለልተኛ መሆን ይጠበቅበታል። የሚሰጣቸው ውሳኔዎችም በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የዳኝነት አካል በይግባኝ ሊታዩ ይገባል።

የሌሎች አገራትም ልምድ እንደሚያሳየው የሲቪል ማኅበራትን በሚያስተዳድሩ አካላት ውስጥ የዘርፉ ተወካዮች ይሳተፋሉ። ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 8 ላይ በመንግሥት ከሚሰየሙት የቦርድ አባላት መካከል ሁለቱ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ከማህበራት የተውጣጡ እነደሚሆን ተመልክቷል። ይህ ውክልና እንዲኖር መደረጉ በራሱ እንደጠንካራ ጎን ሊወሰድ ቢችልም የውክልናው ቁጥር ማነስ ሊታሰብበት ይገባል። እንዲሁም የዚህን አካል ገለልተኛነት ለማጠናከር የቦርዱ ሰብሳቢ በመንግሥትና በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና በማህበራት በጋራ የሚመረጥ ሰው መሆን አለበት። ሥለዚህ የውክልናው አሰላለፍ 3 በመንግሥት የሚሰየሙ የመንግሥት ተወካዮች፤ 3 በበጎ አድራጎት

ድርጅቶችና በማህበራት የሚወከሉ እና አንድ በጋራ ከህግ ወይም ከትምህርት ተቋማት የሚወከል ሰው ቢሆን የቦርዱን ነጻነትና ገለልተኝነት ለማጠናከር ያግዛል፡፡

5. የመሸጋገሪያ ጊዜ

እንደሚታወቀው ቁጥራቸው ከ 3500 በላይ የሚገመቱና በዚህ ህግ ሥር ሊወድቁ የሚችሉ የሲቭል ማኅበራት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ማኅበራት ለረጅም ጊዜ አሁን በሥራ ላይ ያለውን ህግ መሠረት አድርገው የረጅም ጊዜ እቅዶችን ነድፈው በመሥራት ላይ ያሉ ናቸው፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሥራቸው ተጠቃሚ ወገኖች ይገኛሉ፡፡ የሚያንቀሳቅሱት የሃብት መጠንም በተመሳሳይ የሚገመት ነው፡፡ ከሕዝብና ከመንግሥት ተቋማት ጋር የገቧቸው ጊዜን የሚጠይቁ የፕሮጀክት ሥምምነቶች አሉባቸው፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነት ባህርይ ያላቸውን ተቋማት በአጭር ጊዜ ውስጥ በአዲሱ ህግ መሠረት አቋማቸውን እንዲቀይሩ ማስገደዱ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተጠቀሰው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማኅበራቱ የቀድሞ ሥራቸውን መቀጠል የሚችሉ ስለመሆኑ እንኳን በግልጽ አልተመለከተም፡፡ ሥለዚህ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ መርዘም ያለበት ከመሆኑም በላይ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥም ማህበራቱ የቀድሞው ሥራቸውን መቀጠል የሚችሉ ሥለመሆኑ በግልጽ መመልከት አለበት፡፡